የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፷፯
አዲስ አበባ ግንቦት □ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.67
ADDIS ABABA 9 th May, 2016

አዋጅ ቁጥር ፱፻፵/፳፻፰ ዓ.ም

ለከተሞች ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ..ገጽ ፱ሺ፶

Proclamation No.940/2016

International Development Association Financing Agreement for the Urban Productive Safety Net Project Ratification Proclamation …………………………………….. --Page 9050

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፵/፳፻፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣአዋጅ**

ለከተሞች ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፪፻፲፬ ሚሊዮን ፰፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ አስራ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ ጃንዋሪ ፲፪ ቀን ፳ሺ፲፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፳ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 940/2016

**A PROCLMAMTION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENTS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 214,800,000 SDR (two hundred fourteen million eight hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Urban Productivity Safety Net Project was signed in Addis Ababa on the 12th day of January, 2016;

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 5 th day of April 2016;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለከተሞች ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፵/፪ሺ፰"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ ጃንዋሪ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5657-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፲፬ ሚሊዮን ፰፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ አሥራ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት □ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Urban Productive Safety Net Project Ratification Proclamation No. 940/2016".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 5657-ET signed on January 12th 2016, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 214,800,000 SDR (Two Hundred Fourteen Million Eight Hundred Thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter in to force up on its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of May,2016.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDANT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OFETHIOPIA**